| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "የቀለም ፡ ቋት" |
| ርእስ ፤ | "ነገር ፡ በምሳሌ ፤ ..." |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቊ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# የቀለም ፡ ቋት ።

## ነገር ፡ በምሳሌ ፤ ...

---

ከዓለም ፡ ተረቶች ፡ አንድ ፡ ጥርኝን ፡ እናጣጥም ።
(ክፍል ፡ 1)

| ሀገር | ተረት |
|---|---|
| ቻይና | «የሚደርስ ፡ ነገር ፥ አስቀድሞ ፡ ጥላውን ፡ ይጥላል ። » |
| ኢትዮጵያ | «የሚያጠግብ ፡ እንጀራ ፡ ከምጣዱ ፡ ያስታውቃል ። » |
| ማሊ | «የወዳጅ ፡ ቃል ፡ ያስለቅሳል ፤ የጠላት ፡ ቃል ፡ ያሥቃል ። » |
| ኢትዮጵያ | «እንጀራን ፡ ከባዕድ ፥ መከራን ፡ ከዘመድ ። » |
| ቻይና | «ጥሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡ ነው ። » |
| ኢትዮጵያ | «ያፍ ፡ ዘመድ ፥ በገበያም ፡ አይገድ ። » |
| እንግሊዝ | «ብትሥቅ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ዐብሮኽ ፡ ይሥቃል ፤ ብታለቅስ ፡ ግን ፥ ብቻኽን ፡ ታለቅሳለኽ ። » |
| ኢትዮጵያ | «ከወገኑ ፡ የተለየ ፡ አንበጣ ፡ ይኾናል ፡ ፌንጣ ። » |
| ዐረብ | «ባንበሳ ፡ የተመራ ፡ የበግ ፡ መንጋ ፥ በበግ ፡ የተመራን ፡ ያንበሳ ፡ መንጋ ፡ ድል ፡ ያደርገዋል ። » |
| ኢትዮጵያ | «ከ፻፺ ፡ ዳዊት ፥ የልብ ፡ ቅንነት ። » |
| ፊንላንድ | «ትንሽ ፡ ኮከብ ፡ እንኳ ፡ በጨለማ ፡ ያበራል ። » |
| ኢትዮጵያ | «ሰው ፡ ሲታጣ ፥ ይመለመላል ፡ ጐባጣ ። » |
| መስኮብ | «ከእግር ፡ ወለምታ ፡ የምላስ ፡ ወለምታ ፡ ይብሳል ። » |
| ኢትዮጵያ | «ነገር ፡ ሲያመልጥ ፥ ጠጕር ፡ ሲመለጥ ፡ አይታወቅም ። » |
| ናይጄሪያ ፡ | «ሰው ፡ እንደ ፡ በርበሬ ፡ ነው ፤ ካላላመጡት ፡ |
| (ሀውሳ) | መፋጀቱ ፡ አይታወቅም ። » |
| ኢትዮጵያ | «ሰው ፡ በሀገሩ ፡ ሰው ፡ ነው ። » |
| እስራኤል | «ሲ.ቃውንትን ፡ ያላበላ ፡ ማእድ ፡ አልተባረከም ። » |
| ኢትዮጵያ | «ሳይጣሉት ፡ የተጣላ ፥ ሲርብ ፡ ያበላ ። » |
| ኤስፓኛ | «የምንወደው ፡ ካልተገኘልን ፥ እንግዲያው ፡ የሚገኝልንን ፡ እንውደድ ። » |
| ኢትዮጵያ | «አጕንብሶ ፡ በላን ፡ ተኝተኽ ፡ ቀላውጠው ። » |
| ኮንጎ | «ባላባት ፡ የተቀመጠበት ፡ መቀመጫ ፡ አይንቀጠቀጥም ። » |
| ኢትዮጵያ | «አለባለቤቱ ፡ አይነድም ፡ እሳቱ ። » |
| ቻይና | «ቀቅ ፡ ያለ ፡ እግር ፡ ጠማማ ፡ ጫማን ፡ አይፈራም ። » |
| ኢትዮጵያ | «እውነቱን ፡ ተናግሮ ፡ እመሸበት ፡ ያድሯል ። » |
| ናይጄሪያ | «ወንዝ ፥ ምን ፡ ቢረዝም ፥ ምንጩን ፡ አይረሳም ። » |
| ኢትዮጵያ | «ሰው ፡ ቢታጣ ፥ ምድር ፡ ትመሰክር ፡ አፍ ፡ አውጥታ ። » |
| ማላዊ | «ባላባት ፡ እንደቈሻሻ ፡ መጣያ ፡ ነው ፤ ኹሉ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጣል ። » |
| ኢትዮጵያ | «ሰው ፡ መኾን ፡ ዕዳ ፡ ነው ። » |
| ጋና | «ሰውን ፡ የሚያሰጥመው ፡ የረጋውና ፡ ጸጥ ፡ ያለው ፡ ውሃ ፡ ነው ። » |
| ኢትዮጵያ | «ከረጋ ፡ ወተት ፡ ቅቤ ፡ ይወጣዋል ። » |
| ኡጋንዳ | «ቀንድ ፡ ያለው ፡ ያልቻለውን ፥ ቀንደ ፡ ጕዳው ፡ እንዴት ፡ ይቻለው ፧ » |
| ኢትዮጵያ | «ላምን ፡ ቀንዷ ፡ አይከብዳትም ። » |
| ግብጽ | «ወዳጅኽ ፥ ድንጋይ ፡ ብትሰጠው ፡ እንኳ ፡ ይውጥልኻል ፤ ጠላትኽ ፡ ግን ፡ ስሕተትኽን ፡ ይጠባበቃል ። » |
| ኢትዮጵያ | «ጠላት ፡ ይቀባል ፡ ጥላት ። » |
| ሷሂሊ | «እውነቱን ፡ የሚናገር ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ አይሳሳትም ። » |
| ኢትዮጵያ | «ብልኅ ፡ ሲሳሳት ፡ የተራራ ፡ ያኽል ፡ ነው ። » |
| ጀርመን | «ንጹሕ ፡ ኅሊና ፡ ለስላሳ ፡ ትራስ ፡ ነው ። » |
| ኢትዮጵያ | «የሰው ፡ በልቶ ፥ አያድሩም ፡ ተኝቶ ። » |
| ፋርስ | «የሚሰጥም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዝናብ ፡ አይጨነቅም ። » |
| ኢትዮጵያ | «የረጠበ ፡ ሰው ፡ ዝናብን ፡ አይፈራም ። » |
| ፍራንስ | «እውነት ፡ ጫማውን ፡ እስኪያጠልቅ ፥ ውሸት ፡ ዓለምን ፡ አዳርሷል ። » |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

| | |
|---|---|
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «ለወሬ ፡ የለው· ፡ ፍሬ ፤ ላበባ ፡ የለው· ፡ ገለባ ። » |
| ቱርክ | «ሰው· ፡ ዕድልን ፡ አያሥሥም ፤ ዕድል ፡ ግን ፡ ሰው·ን ፡ ታሥሠዋለች ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «ልጃገረድ ፣ ዐሥር ፡ ያጭሽ ፣ አንድ ፡ ያገባሽ ። » |
| ቡ·ል.ጋሪያ | «ዛፍ ፡ ወዳዘሙ፟መበት ፡ ይወድ·ቃል ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «አይተነው· ፡ ጊዜ ፣ ወዳደላበት ። » |
| አየርላንድ | «ው·ሻው· ፡ የኾነው·ን ፡ ቡ·ችላው·ም ፡ ይኾናል ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «ያባያ ፡ ልጅ ፡ ወዳቂ ፣ ያራ፟ኝ ፡ ልጅ ፡ አጥባቂ ። » |
| እንግሊ.ዝ | «ሞት ፡ ዕዳን ፡ ኹሉ· ፡ ይከፍላል ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «የሞተ ፡ ሰው· ፡ ዐንገቱ· ፡ ረዥም ፡ ነው· ። » |
| አየርላንድ | «አንድ ፡ ወሬን ፡ ይዞ ፡ ወዳንተ ፡ የመጣ ፣ ካንተ ፡ ኹለት ፡ ወሬን ፡ ይዞ ፡ ይመለሳል ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «ሰው·ን ፡ ሰው· ፡ ዐማው· ፤ የራሱ·ን ፡ ሳይሰማው· ። » |
| ሮማይስጥ | «ጥሩ· ፡ ብላ ፤ በመጠን ፡ ጠጣ ፤ በደንብ ፡ ተኛ ፤ ከነዚ.ህ ፡ ሦስቱ· ፡ ጤንነት ፡ ይገኛል ። » |
| ኢ.ትዮ·ጵያ | «ጐመን ፡ በጤና ። » |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ 2012 ፡ ዓ.ም. ።